# ንጋት ኢንሹራንስ ብሮከር አክሲዮን ማኅበር

## መመሥረቻ ጽሑፍ

እኛ ከዚህ በታች ስማችን፣ዜግነታችንና፣አድራሻችን ከዚህ በታች የተገለጸው መሥራቾች በኢትዮጵያ ሕግ፣ በተለይም በ1952 ዓ.ም. በወጣው የንግድ ሕግ መሠረት የአክሲዮን ማኅበር ለማቋቋም በመወሰን ይህን መመሥረቻ ጽሑፍ እና ከዚህ ጋር የተያያዘውን የመተዳደሪያ ደንብ አውጥተን የማኅበሩን ካፒታል በስማችን አንጻር የተመለከተውን አክሲዮን ለመግዛት ተስማምተናል::

### አንቀጽ አንድ

### የባለአክሲዮኖች ስም፣ዜግነትና አድራሻ

| ተ.ቁ. | ስም | ዜግነት | አድራሻ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ክልል/ከተማ | ክፍለ ከተማ/ወረዳ | ቀበሌ | የቤት ቁጥር |
| 1. | ክ/ል ትዕግሥቱ ሣህሌ ጊቢ | ኢትዮጵያዊ | አዲስ አበባ | ቦሌ | 02 | 182 |
| 2. | ወ/ሮ ወርቅነሽ መብራቱ ወልዴ | ኢትዮጵያዊት | አዲስ አበባ | ቦሌ | 02 | 182 |
| 3. | ወ/ት አድያም ትዕግስቱ ሣህሌ | ኢትዮጵያዊት | አዲስ አበባ | ቦሌ | 02 | 182 |
| 4. | ወ/ት ሲዲያ ትዕግስቱ ሣህሌ | ኢትዮጵያዊት | አዲስ አበባ | ቦሌ | 02 | 182 |
| 5. | አቶ ኀይለሚካኤል ከምባታ አላካ | ኢትዮጵያዊ | ኦሮሚያ | አድአ | 02 | 1083 |
| 6. | ወ/ሮ አስለፈች ኀ/ስላሴ ተሰማ | ኢትዮጵያዊት | ኦሮሚያ | አድአ | 02 | 1083 |
| 7. | ወ/ት ሲሳይ ኀይለሚካኤል ከምባታ | ኢትዮጵያዊት | ኦሮሚያ | አድአ | 02 | 1083 |
| 8. | አቶ አቤል ኀይለሚካኤል ከምባታ | ኢትዮጵያዊ | ኦሮሚያ | አድአ | 02 | 1083 |

### አንቀጽ ሁለት

### የማኅበሩ መጠሪያ

የማኅበሩ መጠሪያ ስም ንጋት ኢንሹራንስ ብሮከር አክሲዮን ማኅበር ነው::

### አንቀጽ ሦስት

### የማኅበሩ ዋና መ/ቤት

የማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ከተማ፣ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ ቀበሌ 10 የቤት ቁጥር 180 ነው:: ማኅበሩ ሌሎች ቅርንጫፎችን ሊያቋቁም ይችላል::

### አንቀጽ አራት

### የማኅበሩ ዓላማዎች

ማኅበሩ የተቋቋመበት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው::

1. የነባርም ሆነ የታሳቢ ደንበኞች የኢንሹራንስ ፍላጎት መለየትና ማማከር፣ የኢንሹራንስ መግቢያ ዋጋ መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ውል ማዋዋል፣ የውል ዕድሳትና የካሣ ጥያቄዎች መከታተል፣ እና
2. ከማህበሩ ዓላማ ጋር ተዛማጅ የሆኑን ሌሎች ሥራዎችን መሥራት

CamScanner

## አንቀጽ አምስት

## የማኅበሩ ዋና ገንዘብ

1. የማኅበሩ የተፈረመ ካፒታል ብር 50,000.00 /በፊደል ሃምሳ ሺህ/ ነው:: ከዚሁ ውስጥ ብር 17,000.00 (አስራ ሰባት ሺ) ተከፍሏል:: ቀሪው ብር 33,000.00 (ሰላሳ ሶስት ሺ) ከሚያዝያ 1 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ በአለው ዓመት በየሩብ ዓመቱ በአራት እኩል ክፍያዎች ይከፈላል::

2. የማኅበሩ የተፈረመ ካፒታል እያንዳንዳቸው ብር 1,000/አንድ ሺ/ ዋጋ ባላቸው በጠቅላላው 50 /በፊደል ሃምሳ / ተራ አክሲዮኖች ተደልድሏል::

3. የማኅበርተኛ የአክሲዮን ድርሻ የመዋጮ መጠን እንደሚከተለው ተገልጿል::

| ተ.ቁ. | ስም | የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት | በገንዘብ | የተከፈለ | | ቀሪ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በአክሲዮን ድርሻ | የመዋጮ መጠን በብር | የአክሲዮን ድርሻ | የመዋጮ መጠን |
| 1. | ኮ/ል ትዕግሥቱ ሣህሌ ጊቤ | 25 | 25,000.00 | 7 | 7,000.00 | 18 | 18,000.00 |
| 2. | ወ/ሮ ወርቅነሽ መብራቱ ወልዴ | 2 | 2,000.00 | 1 | 1,000.00 | 1 | 1,000.00 |
| 3. | ወ/ት አድያም ትዕግስቱ ሣህሌ | 2 | 2,000.00 | 1 | 1,000.00 | 1 | 1,000.00 |
| 4. | ወ/ት ሊዲያ ትዕግስቱ ሣህሌ | 1 | 1,000.00 | 1 | 1,000.00 | - | - |
| 5. | አቶ ኀይለሚካኤል ከምባታ አላካ | 16 | 16,000.00 | 4 | 4,000.00 | 12 | 12,000.00 |
| 6. | ወ/ሮ አሰለፈች ኀ/ስላሴ ተሰማ | 2 | 2,000.00 | 1 | 1,000.00 | 1 | 1,000.00 |
| 7. | ወ/ት ሲሳይ ኀይለሚካኤል ከምባታ | 1 | 1,000.00 | 1 | 1,000.00 | - | - |
| 8. | አቶ አቤል ኀይለሚካኤል ከምባታ | 1 | 1,000.00 | 1 | 1,000.00 | - | - |

## አንቀጽ ስድስት

## አክሲዮኖች

የማኅበሩ አክሲዮኖች ከአንድ እስከ ሃምሳ ቁጥሮች ተሰጥቶአቸዋል::

## አንቀጽ ሰባት

## የባለ አክሲዮኖች ኃላፊነት

ባለ አክሲዮኖች ኃላፊነታቸው በማኅበሩ ውስጥ ባላቸው የአክሲዮን ድርሻ ልክ ነው::

## አንቀጽ ስምንት

## የሂሳብ ዓመት

የሂሳብ ዓመቱ የሚጀምረው ከሐምሌ 1 ጀምሮ ሲሆን የሚያልቀው ሰኔ 30 ቀን በየዓመቱ ነው:: ሆኖም የመጀመሪያው የሂሳብ ዓመት የሚጀምረው ማኅበሩ ሥራ ከጀመረበት እስከ ሰኔ 30 ቀን ይሆናል::

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 52
CamScanner

አንቀጽ ዘጠኝ

የትርፍ አከፋፈል

1. በየሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ የማኅበሩን ንብረት እና ዕዳ የሚያሳይ የሂሳብ ሚዛን/ ባላንስ ሺት/ ተዘጋጅቶ ለዲሬክተሮች ቦርድ ይቀርባል፡፡

2. የማኅበሩ ዓመታዊ የሂሳብ ሁኔታ የሚያሳዩ ሰነዶች፣ማለትም የሂሳብ ሚዛን /ባላንስ ሺት/፣የትርፍና ኪሳራ መግለጫ፣ የንብረት ቆጠራ፣የዲሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት እና የኦዲተሮች ሪፖርት በማኅበሩ መዝገብ ላይ ለተመዘገቡ ባለአክሲዮኖች ቢያንስ ከመደበኛው ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ቀን 15 ቀን አስቀድሞ በሪኮማንዴ ይላካል፡፡

3. ከዚህ በታች ከንዑስ አንቀጽ 4/ሀ እና ለ / ሥር የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆነው በዓመቱ ሂሣብ መግለጫ ውስጥ እንደተመለከተው የማኅበሩ የዓመቱ የተጣራ ትርፍ፣ጠቅላላ ወጪና፣አላቂ ለሚሆኑ ነገሮች መተኪያ ገንዘብ /አሞርታይዜሽን/፣አላዋንስ እና ለሌሎች መዋጮዎች ታክስና ያለፈው ዓመት ግዴታዎች ከተቀነሱ የሚታየው የተጣራ ትርፍ ነው፡፡

4. ከተጣራው ዓመታዊ ትርፍ ላይ፡-

   ሀ. የጠቅላላ የካፒታሉን 20% እስከሚያክል ድረስ በየዓመቱ 5% ለሕጋዊ መጠባበቂያ ይያያዛል፡፡

   ለ. በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ የጸደቁ ሌሎች ልዩ የመጠባበቂያ ሂሣቦችና የአሞርታይዜሽን ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ ተራፊው በተከፈለው የአክስዮን ድርሻ ልክ ለባለ አክስዮኖች ይከፋፈላል፡፡

አንቀጽ አሥር

የማኅበሩ የአስተዳደር ክፍሎች፣

ሀ. የባለአክስዩኖች ጠቅላላ ጉባዔ፣

ለ. የዲሬክተሮች ቦርድ፣እና

ሐ. ሥራ አስኪያጅ ናቸው፡፡

አንቀጽ አሥራ አንድ

ጠቅላላ ስብሰባ

የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ነው፡፡ ይህም ጉባዔ መደበኛና ድንገተኛ ስብሰባ የሚኖሩት ሲሆን በደንቡና በንግድ ሕግ መሠረት

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 52

ሀ. የዲሬክተሮች ቦርድ አባላትን ከመካከሉ ይመርጣል፣ይሾማል፣ ይሽራል::

ለ. የውጭ ኦዲተሮችን ይሾማል፣ ይሽራል፣አበላቸውንም ይወስናል::

ሐ. ሌሎች በህግና ማኅበሩ ህጎች መሠረት ለጠቅላላ ጉባዔ የተፈቀዱ ተግባሮች ያከናውናል::

## አንቀጽ አሥራ ሁለት

## የዲሬክተሮች ቦርድ

1. ማኅበሩ የሚተዳደረው በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በሚመረጡ ቢያንስ 3 አባሎች ቢበዛ 7 ባሉት የዲሬክተሮች ቦርድ ነው:: የቦርዱም የስራ ዘመን 3 ዓመት ነው::
2. የማኅበሩ የመጀመሪያ የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚከተሉት ናቸው::

    1. ወ/ት አድያም ትዕግስቱ ሣህሌ
    2. ኮ/ል ትዕግስቱ ሣህሌ ገ.ቢ. — ሰብሳቢ
    3. አቶ ኃይለሚካኤል ከምባታ አላኪ — አባል
    4. ወ/ት ሊዲያ ትዕግስቱ ሣህሌ — አባል
    5. ወ/ት ሲሳይ ኃይለሚካኤል ከምባታ — አባል
    6. አቶ አቤል ኃይለሚካኤል ከምባታ — አባል

    አባል

3. የዲሬክተሮች ቦርድ ከአባሎቹ አንዱን ፕሬዝዳንት አድርጎ ይመርጣል::
4. ወ/ት አዲያም ትዕግስቱ የዲሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው ተመርጠዋል::
5. የዲሬክተሮች ቦርድ አባል የተመረጠበት ጊዜ ካበቃ እንደገና ሊመረጥ ይችላል::
6. ዲሬክተር መለወጥ ቢያስፈልግ የንግድ ሕግ ቁጥር 351/ አስተዳዳሪ ስለመለወጥ / ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል:: ዲሬክተሩ ከሥራው ላይ ቢቀር የንግድ ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል:: ሆኖም ከሥራው ላይ የቀረ ዲሬክተር በሌላ ዲሬክተር ያልተወከለን ዲሬክተር ለመወከል ይችላል::
7. እያንዳንዱ የተመረጠ ዲሬክተር የሥራ ጊዜው እስከሚፈፀም በማኅበሩ የተመዘገበ አንድ አክሲዮን ያስይዛል:: የሥራ ... በንግድ ሕግ ቁጥር 349 ስር በተገለጸው ሁኔታ ይመለስ... ... ንግድ ሕግ ቁጥር 349 እና 360 ድንጋጌ መሠረት የዲሬክተሮች ምዝገባ ይ...ል::
8. በንግድ ሕግ ቁጥር 362፣364፣446 እና447 ሥር የተገለጹት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የዲሬክተሮች ቦርድ ከዚህ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል::

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

ሀ. የማኅበሩን አስተዳደር መቆጣጠር፣

ለ. በጠቅላላው የባለአክሲዮች ስብሰባ ከተወሰነው ጊዜ ሳያልፍ የማኅበሩን የንግድ ሥራ ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ፣

ሐ. ማኅበሩን ሥራ አስኪያጅ /ጆች/ ለመሾም እንደአስረላጊነቱ ፀሐፊዎችን፣ ሠራተኞችን ለመቅጠር፣ ለማሰናበትና ለማገድ እንዲሁም ደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችንና የሥራ ሁኔታዎችን መወሰን፣

መ. የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ማፍራትና መሸጥ፣

ሠ. በአገር ውስጥ ከሚገኝ ማንኛውም ባንክ የገንዘብ ድርጅት ወይም ተቋም ለማኅበሩ ዓላማዎች ማከናወኛ የሚውል ብድር በመያዣ ወይም ያለመያዣ መበደር፣መደራደር፣ መዋዋልና መፈረም፣

ረ. ተጨማሪ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማቋቋምን መወሰን፣

ሰ. ማናቸውንም ተስማሚ ሆኖ ያገኘውንና የማኅበሩን ገንዘብ ሥራ ላይ ስለማዋል ሃሳብ ለጠቅላላ የባለ አክሲዮኖች ስብሰባ ማቅረብ፣

9. የዲሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ሥልጣኑን ለሰብሳቢው ለመስጠት ይችላል::

10. ሥራ አስኪያጅ እና ማናቸውም ሌላ በዲሬክተሮች ቦርድ ሥልጣን የተሰጠው ዲሬክተር በማኅበሩ ስም ሊፈርም ይችላል፣ የዲሬክተሮች ቦርድ በአንድነት ወይም በነጠላ ማኅበሩ ስም ለመፈረም የሚችሉ ተጨማሪ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሥራ አስኪያጆችን ለመሾም ይችላል::

11. አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የዲሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ሰብሳቢው ወይም በሥራ አስኪያጁ ሊጠራ ይችላል:: የዲሬክተሮች ስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚታተም ሕጋዊ ጋዜጣ ሊደረግ ይችላል:: ዲሬክተሮች የማኅበሩን ሥራ ያካሂዳሉ፣ ውሳኔአቸውም በንግድ ሥጉ አንቀጽ 358 ድንጋጌ መሠረት ይመዘገባል::

12. የዲሬክተሮች ቦርድ ፀሐፊ ይሾማል:: የዲሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎች በሰብሳቢውና በጸሐፊው ተፈርመው በቃለ ጉባኤ መዝገብ ውስጥ ተመዝግበው ይቀመጣሉ::

13. ቦርዱ በክፉ ልቦና፣ በተንኮል ወይም ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ ካልሠራ በቀር የተጣለበትን ኀላፊነት በመወጣት ወይም በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት በገኘው ሥልጣን ለስራው ሥራ በሕጋዊ መንገድ ላከናወኑት በግል ምንም ኃላፊነት አይኖርበትም::

14. የማኅበሩ ዲሬክተሮች በማንኛውም ሁኔታ ከማኅበሩ ገንዘብ ሊበደሩ ወይም ለግል ዕዳቸው በማኅበሩ ሊጠቀሙ አይችሉም::

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 52

The FDRE Ministry of ...

15. የዲሬክተሮች የአገልግሎት ክፍያ በየዓመቱ በመደበኛ ጠቅላላ ስብሰባ ይወሰናል፡፡ ይህም ክፍያ ከጠቅላላ ወጪ ውስጥ ይጠቃለላል፡፡

## አንቀጽ አሥራ ሦስት

### ሥራ አመራር

1. የማኅበሩ የአስተዳደር ሥራ የሚመራው በዲሬክተሮች ቦርድ ተመርጦ የሚሾም የአገልግሎት ክፍያው እና አገልግሎት የሚሰጥበት ሁኔታ የሚወሰንለት ዋና ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፡፡

2. ዋና ሥራ አስኪያጅ በመመሥረቻ ጽሑፍ፣ በመተዳደሪያ ደንብ እና የዲሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው መመሪያዎች መሠረት የማኅበሩን ሥራዎች ይሠራል፣ ማናቸውንም ለማኅበሩ ሥራ አስፈላጊ የሆኑትን ተግባሮች ያከናውናል፡፡

3. አቶ ኀይለሚካኤል ከምባታ አላካ የአክሲዮን ማኅበሩ የመጀመሪያው ሥራ አስኪያጅ ሆነው ተሹመዋል፡፡

## አንቀጽ አሥራ አራት

### ተቆጣጣሪዎች/ ኦዲተሮች/

1. ማኅበሩ በየዓመቱ በሚደረገው ጠቅላላ ስብሰባ ኦዲተር ወይም ኦዲተሮች ይሾማል፡፡ የሚሾመው ኦዲተር ወይም ኦዲተሮች በሂሳብ ምርመራ ሥራ የተረቀደለት ሰው ወይም ድርጅት ይሆናል፡፡ የነዚህም ኦዲተሮች ተግባር ስልጣንና ኀላፊነት በሕግና በተለይም በንግድ ሕጉ ቁጥር 368 እና 460 መሠረት ይሆናል፡፡

2. የኦዲተሮች የአገልግሎት ዋጋ በማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ አሥራ አምስት

### የማኅበሩ ቆይታ

ማኅበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ሲሆን በንግድ ሕጉ ቁጥር 495 ሥር በተገለጹት ምክንያቶች ሊፈርስ ይችላል፡፡

NATIONAL BANK 52

CamScanner

## አንቀጽ አሥራ ስድስት

## የማኅበሩ የሥራ ሪፖርት

1. እያንዳንዱ የሂሳብ ማጠቃለያ በሚዘጋበት ጊዜ የዲሬክተሮች ቦርድ በማኅበሩ ያሉትን ልዩ ልዩ ንብረቶችና ዕዳዎች የሚያመለክትና የንብረቱን ዝርዝር የሚይዝ መዝገብ ያደራጃል::

2. ዲሬክተሮች የዓመቱን የሂሣብ ሚዛን የትርፍና ከሣራ መግለጫ እንዲሁም ባለፈው የሂሳብ ማጠቃለያ ሥራ ጊዜ ስለ ማኅበሩ ሁኔታና አሠራር ሪፖርት ያደራጃሉ::

3. ለጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ከመደረጉ አሥር ቀን በፊት የንብረት ዝርዝር መዝገብ፣ የሂሳብ ሚዛን፣ ትርፍና ኪሣራ ሂሳብ፣ የዲሬክተሮች ሪፖርት ለኦዲተር ተዘጋጅተው መሰጠት አለባቸው፣ በዚህ ጊዜ እነዚሁ ሰነዶች ለሚመለከተው ንግድ ሚኒስቴር መተላለፍ አለባቸው::

## አንቀጽ አሥራ ሰባት

## ጠቅላላ

በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ ውስጥ ባልተገለጹት የማኅበሩ ጉዳዮች ላይ ሁሉ እንደ አስፈላጊነቱ የንግዱ ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ::

ይህ የመመሥረቻ ጽሑፍ ዛሬ ተፈረመ::

በመሥራች አባሉችና ፈራሚዎች በአዲስ አበባ ከተማ

| የአባላቱ ስም | ስምና ፊርማ |
|---|---|
| 1. ኮ/ል ትዕግስቱ ሣህሉ ጊቤ | [signature] |
| 2. ወ/ሮ ወርቅነሽ መብራቴ ወልዴ | [signature] |
| 3. ወ/ት አድያም ትዕግስቱ ሣህሉ | [signature] |
| 4. ወ/ት ሊድያ ትዕግስቱ ሣህሉ | [signature] |
| 5. አቶ ኀይለሚካኤል ከምባታ አላካ | [signature] |
| 6. ወ/ሮ አስለፈች ኀይለ ስላሴ ተሰማ | [signature] |
| 7. ወ/ት ሲሳይ ኀይለሚካኤል ከምባታ | [signature] |
| 8. አቶ አቤል ኀይለሚካኤል ከምባታ | [signature] |

The FDRE Ministry of Justice ... Authentication and Registration Office (stamp)
National Bank (stamp)

CamScanner

በኢፌዴሪ የፍትህ ሚኒስቴር
የሰነዶች ማ... ቤት
አዲስ አበ (ዋናው መሥሪያ ቤት)

ቁጥር ቃመጋ/5199/14ሀ/ህ
በጽሕፈት ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል።

አዲስ አበባ 22 9 ቀን 2ዐ...ዓ.ም.

ያርጋ ታደሰ
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ
ጽ/ቤት ኃላፊ

በኢፌዴሪ የፍትህ ሚኒስቴር የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት-ሐ
FDRE Ministry of Justice ... Authentication and Registration ...

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

የቴምብር ቀረጥ ማረጋገጫ ማኅተም

...ከፈለበት ሰነዶች ______
... ልክ ብር 566
______
...ብር የሆነ ቴምብር ተለጥፏል።
...ቁጥር 292981
2219 ቀን 2ዐ 03 ዓ.ም
የቴምብር ቀረጥ መብት አስፈጻሚ
ኦርባሕ